# በ BPS ውስጥ ለብዝሃ ቋንቋ ተናጋሪ ተማሪዎች መዋቅራዊ ተግዳሮቶች

**ከ ELL ግብረ ኃይል የወላጆችና ተንከባካቢዎች አውድ**

ሜይ 4/2023

# በቦስተን የሕዝብ ትምህርት ቤቶች የሚማረው ማነው?




## ግማሹ የBPS ተማሪዎች ብዝሃ ቋንቋ ተናጋሪዎች ወይም እንግሊዘኛ በመማር ላይ ናቸው።

**(በግራ በኩል ያለው የፓይ ቻርቱ አረንጓዴ ክፍሎች)**

የዲስትሪክቱ አጠቃላይ ምዝገባ ላለፉት 5 አመታት እየቀነሰ ባለበት ወቅትም ቢሆን የብዝሃ ቋንቋ ተማሪ/እንግሊዘኛ ተማሪ (ML/EL) በያዝነው አመት 2022-2023 በትንሹ እድገትን አሳይቷል።

ከበጀት/የእቅድ አቀራረቦች ወደ ELLTF የተገኘ መረጃ 2/9/23; DESE የትምህርት ቤት መግለጫዎች

# የአሁኑ የBPS እንግሊዝኛ ተማሪዎች/ብዝሃ ቋንቋ ተናጋሪዎች ምን ቋንቋዎች ይናገራሉ?




- ከግማሽ በላይ የሚሆኑ የእንግሊዝኛ ተማሪዎች/ብዝሃ ቋንቋ ተናጋሪዎች ስፓኒሽ ይናገራሉ።
- 97% ያህሉ ከ 10 ዋና ዋና ቋንቋዎች አንዱን የሚናገሩ ናቸው።

በማርች 2022 የተወሰደ የበጀት/የእቅድ ELLTF 2/9/23 የቀረበ መረጃ

የብዙ ቋንቋና የብዝሃ ባህላዊ ትምህርት ቢሮ የመጀመሪያዎቹ ሁለት ስልታዊ ቅድሚያ የሚሰጣቸው ናቸው

- ተማሪዎች **የስቴት የሁለት ቋንቋ ማንበብና መጻፍ ማህተም** ማግኘት እንዲችሉ **የሁለት ቋንቋ ፕሮግራሞችን ማስፋት**፣ እና
- የአካል ጉዳት ላለባቸው EL/ML ተማሪዎች **የአፍ መፍቻ ቋንቋ አገልግሎቶችን ተደራሽነት ማስፋ**።



# ተማሪዎች በየትኛው ፕሮግራሞች ውስጥ ይማራሉ?

**ELD1-3s**

የእንግሊዘኛ ቋንቋ እድገት 1-3 (ELD 1-3s) ላይ ለሚገኙ ተማሪዎች **ግማሽ ያህሉ ለእንግሊዘኛ ተማሪዎች/ብዝሃ ቋንቋ ተማሪዎች በፕሮግራም** ውስጥ ይገኛሉ። ቀሪው ግማሽ ደግሞ በጠቅላላ ትምህርት ውስጥ ነው።







**ELD4-5s**

የእንግሊዘኛ ቋንቋ እድገት ደረጃ 4-5 (ELD 4-5s) ላይ የሚገኙ ተማሪዎች ሁሉም በአጠቃላይ ትምህርት (ከ4 ተማሪዎች በስተቀር) ውስጥ ይገኛሉ።

በማርች 2023 ከበጀት/እቅድ የተገኘ መረጃ

# የተማሪዎች መምህራን ቋንቋቸውን ይናገራሉ?

አይናገሩም። አብዛኞቹ የእንግሊዝኛ ተማሪዎች/ብዝሃ ቋንቋ ተናጋሪዎች ቋንቋቸውን የሚናገር መምህር የለም።
ዲስትሪክቱ ለሁሉም መምህራን አጠቃላይ የቋንቋ መረጃ ወይም ቅልጥፍናን ለመገምገም መደበኛ ሂደት አሁን ላይ የለውም።




ግማሹ ELD1-3s እና 100% ELD4-5s በእነዚህ መምህራን ስር የሚማር ነው

የSEI ፕሮግራሞች ከሁሉም ELD 1-3s 41% ያህሉን ያስተምራሉ

SLIFE ፕሮግራሞች ከሁሉም ELD1-3s 3% ያህሉን ያስተምራሉ

የጣምራ ቋንቋ ፕሮግራሞች ከሁሉም ELD1-3s 7% ያህሉን ያስተምራሉ

መረጃው በኤፕሪል 2022 ከ BPS የተገኘ ነው

# ቀደም ብለው በነበሩት 3 አመታት ውስጥ፣ የእንግሊዝኛ ቋንቋ ተማሪዎች ከ 1-3 (ELD1-3s) የእንግሊዝኛ ቋንቋ ተማሪዎች/የብዝሃ ቋንቋ ተማሪዎች ከ SEI ቋንቋ-ተኮር እንዲሁም ወደ አጠቃላይ ትምህርት ክፍሎች ተሸጋግረዋል።




**አሁን ላይ ወደ 1,000 ELD1-3 ገደማ የሚሆኑ ተማሪዎች በአጠቃላይ ትምህርት ውስጥ እንዳሉ የምንገምት ሲሆን እነዚህም የተማሪ ምደባ በ 2019-2020 ካለው ጋር ተመሳሳይነት ቢኖረው ኖሮ በ SEI ውስጥ ይገኙ ነበር።**

በማርች 2023 ከበጀት/እቅድ የተገኘ መረጃ

# በ SEI ላይ የሚገኙ ተማሪዎች ቋንቋቸውን ከሚናገሩ ሌሎች ተማሪዎች ጋር በቡድን እየተቀመጡ አይደሉም፡፡

በ SEI ውስጥ ከሚገኙ ተማሪዎች፣ አዝማሚያው ብዙዎቹ በቋንቋቸው ከሚናገሩ ተማሪዎች ጋር ክፍል ከመሄድ ይልቅ (ከአንድ በላይ የተማሪ ቋንቋ በአንድ ላይ ተሰባስበው በሚገኙባቸው ክፍሎች) **በ "SEI ብዝሃ ቋንቋ" እየተመደቡ** ነው፡፡

**ተጨማሪ SEI ባለብዙ ቋንቋ፣ ያነሰ SEI ቋንቋ-ተኮር**
እንደ ሁሉም የSEI ምዝገባዎች መቶኛ




በማርች 2023 ከበጀት/እቅድ የተገኘ መረጃ

| በ2022-2023 በ SEI ብዝሃ በተመዘገቡ ተማሪዎች የሚነገሩ ቋንቋዎች | | |
|---|---|---|
| **BPS SEI ያቀርባል በእነዚህ ቋንቋዎች ውስጥ ያሉ ቋንቋ-ተኮር ፕሮግራሞች** | ኬፕ ቨርዴያን ክሪኦል | 5% |
| | ቻይንኛ | 2% |
| | ሃይቲ ክሪኦል | 7% |
| | ስፓኒሽ | 53% |
| | ቬትናምኛ | 4% |
| | | **71%** |
| **BPS በእነዚህ ቋንቋዎች SEI ቋንቋ-ተኮር ፕሮግራሞችን አይሰጥም** | አረብኛ | 3% |
| | እንግሊዘኛ | 5% |
| | ፈረንሳይኛ | 1% |
| | ፖርቱጋልኛ | 13% |
| | ሶማልኛ | 1% |
| | ሌላ | 5% |
| | | **29%** |

በSEI መልቲ ቋንቋ፣ የተለያዩ ቋንቋዎች ተናጋሪዎች በአንድ ላይ በክፍል ውስጥ ተደባልቀው ይገኛሉ፡፡ በፕሮግራሙ ውስጥ ከሌሎች ቋንቋቸውን ከሚናገሩ ጋር ክፍል ውስጥ 71% **ተማሪዎች ለቋንቋ-ተኮር ምደባ ብቁ ናቸው፡፡**

**53% የ SEI ብዝሃ ቋንቋ ምዝገባዎች ስፓኒሽ ተናጋሪዎች ናቸው፡፡**
የስፓኒሽ ተናጋሪ ELD1-3 ተማሪዎች ቁጥር ቀደም ብለው በነበሩት 5 አመታት በ 19 በመቶ ያደገ ቢሆንም ነገር ግን ስፓኒሽ ተናጋሪ ቋንቋ-ተኮር SEI (እና ባለሁለት ቋንቋ) ምዝገባ በተመሳሳይ ጊዜ በ 2 በመቶ መቀነስ አሳይቷል፡፡

በማርች 30/2023 ከበጀት/እቅድ የተገኘ መረጃ

# አሁን ላይ የ EL/ML መርሃ ግብሮች ተማሪዎች በሚኖሩበት አካባቢ መቀመጡን ለማረጋገጥ ወይም ተማሪዎች በቤታቸው ላይ የተመሰረተ ምደባ ዞን ላይ ባይሆኑም እነዚያን ፕሮግራሞች ማግኘት እንደሚችሉ የማረጋገጥ እቅድ የለም።

ለምሳሌ፣ ቀደም ብለው በነበሩት አምስት አመታት፣ በክላስተር E – የ BPS ዲስትሪክት የሮክስበሪ፣ ዶርቼስተርና ማታፓን ክፍሎች እየቀነሰ የሚሄድ፣ ለስፓኒሽ ተናጋሪ ELD1-3s ከ 9-12ኛ ክፍል ምዝገባ በእጥፍ መጨመር አሳይቷል።

ይህ የከተማው ክፍል ለስፓኒሽ ተናጋሪዎች ቋንቋ-ተኮር የመማሪያ ክፍሎች አብረውት የሉም። እነዚያ ተማሪዎች በባለብዙ ቋንቋ ፕሮግራሞች ውስጥ ተመድበዋል።




ከ 3/30/23 የበጀት/እቅድ የተገኘ መረጃ

# በ SEI ቋንቋ-ተኮር ፕሮግራሞች ላይ ጥቂት የእንግሊዝኛ ተማሪዎች/በብዝሃ ቋንቋ ተናጋሪዎች ቢመደቡ ለምን ለውጥ ያመጣል?

**SEI "የተቀነሰ" ፕሮግራም አይደለም፤** ይህም ማለት ተማሪዎች እንግሊዘኛ በሚማሩበት ጊዜ **የአፍ መፍቻ ቋንቋ ችሎታቸውን ያጣሉ**?

**አዎ ያጣሉ**።

## ቢሆንም፤ አሁን ላይ SEI ቋንቋ-ተኮር ፕሮግራሞች በ BPS ውስጥ አስፈላጊ ናቸው።

1. ቋንቋ-ተኮር ክፍል ውስጥ የሚገኙ ተማሪዎች ቋንቋቸውን መምህራቸው ባይናገሩም እንኳ **የነሱን ቋንቋ የሚናገሩ እኩዮች** ይኖሯቸዋል።
2. SEI ቋንቋ-ተኮር ፕሮግራሞች በቋንቋ ተማሪዎችን ለማቧደን ሲሆን ይህም **የአፍ መፍቻ ቋንቋ ተደራሽነትን ለማሳደግ አስፈላጊ የሆነው የዲስትሪክቱ ተቋም ቁልፍ አካል** ሲሆን በሁለት ቋንቋዎች መማርና ማንበብ መቻልን ወደሚደግፉ ፕሮግራሞች የሚወስድ ነው።

# አብዛኛዎቹ የእንግሊዘኛ ተማሪዎች/ብዝሃ ቋንቋ ተናጋሪዎች የአካል ጉዳተኛ ተማሪዎችም ናቸው።

**ሁሉም የእንግሊዘኛ ተማሪዎች/ብዝሃ ቋንቋ ተናጋሪዎች ወደ 1/4 የሚጠጉ የአካል ጉዳተኛ ተማሪዎች ናቸው**




## ሁሉም አካል ጉዳተኛ ተማሪዎች

**ከ1/3 በላይ የሚሆኑት የእንግሊዘኛ ተማሪዎች/የብዙ ቋንቋ ተማሪዎች ናቸው**




ከበጀት/እቅድ፣ ማርች 2022 እና ኤፕሪል 2022 የተገኘ መረጃ፤ የDESE ትምህርት ቤት መገለጫዎች

**የአካል ጉዳት ያለባቸው የእንግሊዘኛ ተማሪዎች በማደግ ላይ ያሉ የሕብረተሰብ ክፍሎች ናቸው**




Data received from Budget/Planning, 3/30/23

**የአፍ መፍቻ ቋንቋ መዳረሻ የለም** -- የአካል ጉዳት ያለባቸው የእንግሊዘኛ ተማሪዎች መምህራኖቻቸውና አቅራቢዎቻቸው ቋንቋቸውን ለመናገር ዋስትና የላቸውም።

# የእንግሊዘኛ ተማሪዎች/የብዝሃ ቋንቋ ተማሪዎች ተለይምም ደግሞ  የ ኤEL/ML  አካል ጉዳተኛ ተማሪዎችበ MCAS ያላቸው ውጤት ዝቅተኛ ነው።







የ BPS መረጃ፣ በልግ 2021

# ለ2023-2024 አዲስ የበጀት ድልድል የተማሪዎችን የአፍ መፍቻ ቋንቋ ድጋፍ ተደራሽነት ለማስፋት ብዙም የሚያግዝ አይደለም።

**በሁለት ቋንቋ ፕሮግራሞች ምዝገባ ላይ ለሌሉ 15,600 ML/Els፣ የአፍ መፍቻ ቋንቋ ተደራሽነትን ለማስፋት የዲስትሪክቱ እቅድ የለም።**

የ2023-2024 በጀት **ለሁለት ቋንቋ ፕሮግራሞች የረዥም ጊዜ እቅድ አዲስ ግብአቶችን** አካቶ ይዟል። በነዚያ ፕሮግራሞች ውስጥ 7% የሚሆኑት የብዝሃ ቋንቋ ተማሪዎች/የእንግሊዘኛ ተማሪዎች ብቻ ናቸው።

*አብዛኛዎቹ የ BPS ተማሪዎች በሁለት ቋንቋ መርሃግብሮች ላይ ከመድረሳቸው በፊት ብዙ አመታት ይወስድባቸዋል።*

በ 2023-2024 የበጀት ፈንድ 38 አዲስ **የ ESL መምህር የስራ መደቦች** ተፈጥረዋል።

*ተማሪዎች የአፍ መፍቻ ቋንቋ ድጋፍ ተደራሽነት ውስን በሆነባቸው የፕሮግራም አካባቢዎች የሰው ኃይልን  አቅርቦት እንዲሰፋ ያደርጋል።*

**ሁሉም ተማሪዎች በሁለት ቋንቋ ማንበብና መጻፍ ማኅተም እንዲቀበሉ ለማድረግ ራዕይ እንፈልጋለን**



የተግባር የቋንቋዎች ጥናት ማእከል፣ “በቦስተን የሕዝብ ትምህርት ቤቶች የሁለት ቋንቋ ፕሮግራሞች ግምገማ ያስፈልገዋል፡ ዲስትሪክቱ የሁለት ቋንቋ ፕሮግራሞችን መቀጠልና መስፋፋት እንዴት ሊደግፍ ይችላል?” ኖቬምበር 2021

# ወላጆችና ተንከባካቢዎች፡ ተሞክሮዎ ምን ይመስላል?

1. **ልጅዎ የሚገኘው በየትኛው የእንግሊዝኛ ተማሪ ፕሮግራም ውስጥ ነው?**
   ሀ. እንግሊዘኛ ገና የማይናገር ልጅ ስላሉት ውጤታማ **ፕሮግራሞች** እንዴትና ምን ተማራችሁ?
   ለ. የልጅዎ ትምህርት ቤት ለቤትዎ ምን ያህል **ተደራሽ** ነው?
   ሐ. ከልጅዎ መምህርና ከሌሎች የስራ ባልደረቦች ጋር ምን ያህል **መግባባት** ይችላሉ?

2. **ልጅዎ በትምህርት ቤት ውስጥ እንዴት ነው?**
   ሀ. የልጅዎ እንግሊዝኛ የመማር ተሞክሮ ምን ይመስላል? ስኬቶች፣ ተግዳሮቶች?
   ለ. በቤት ውስጥ የሚነገር ቋንቋዎን በመጠበቅ ረገድ ልጅዎ እንዴት እየሆነ ነው? ስኬቶች፣ ተግዳሮቶች?

3. **ልጅዎ የልዩ ትምህርት አገልግሎቶችን የሚያገኝ ከሆነ፣ እርስዎና ልጅዎን ከሚያስተምሩና ከሚደግፉ ሰራተኞች ጋር ምን ያህል መግባባትን መፍጠር ይችላሉ?**